እ.ኢትዮ.አ. የካቲት 12 ቀን 2002ዓ.ም.
ጃንዋሪ 19/2010

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

ለሕጋዊው ቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት ፤
ካሊፎርኒያ

በሲያትል ለመንበረ-ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል መንበረ-ጵጵስና ጽሕፈት ቤት፤
ሲያትል

የብጹዕ አባታችንን የአቡነ ዜና ማርቆስን ዕረፍት በተመለከተ የተሰማንን እጅግ ጥልቅና መሪር የሆነ ሐዘናችንን ስንገልጽ፤ ለቤተ-ክርስቲያንና ለእኛም የቤተ-ክርስቲያን ልጆች ቸሩ አምላካችን እግዚአብሄር ብርታቱንና ጽናቱን እንዲሰጠን በጸሎት በመጠየቅ ነው።

ክብር ይግባውና ጌታችን፣ አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ  በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ቁጥር 16 «...መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ። ...» በማለት እንደ ተናገረው፤ የብጹዕ አባታችንም መልካም ሥራቸው ከቅድስት ሃገር ከኢትዮጵያ ጀምሮ እስከ ውጭ ሃገር ድረስ በሰፊው እየታየና እያንፀባረቀ ለትውልድ እየተላለፈ ይገኛል።

እንግዲህ ብጹዕ አባታችን ለጊዜው ከኛ በአጸደ-ነፍስ ቢለዩም በእግዚአብሄር ፊት ሕያው ናቸው፤ የድካማቸውንም ዋጋ መኮንነ-ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት የብርሃን አክሊል አቀዳጅቶ ይከፍላቸዋል ።

ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 9«...የምንሞት ስንመስል እነሆ ሕያዋን ነን።...» በማለት በሰፊው የገለፀው፤ ለጊዜው በሞት በአጸደ-ሥጋ ብንለይ በእግዚአብሄር ፊትና በሰማያዊው ቤታችን ሕያዋን መሆናችንን ነው።

ጌታችንም፦ «...ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ። የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳን ሕያው ይሆናል።ሕያው የሆነ ሁሉ ለዘላለም አይሞትም ...» ዮሐ.11፥25-26 ሲል ስለ ትንሳኤና ሕይወት አስተምሮናል ።

ስለዚህ ማጽናናት ባሕርዩ የሆነው አምላካችን ለብጹዓን አባቶቻችን ለሊቃነ-ጳጳሳት፣ ለአበው ካህናት፣ ለዲያቆናት፣ ለመላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ምዕመናንና ምዕመናት መጽናናቱን እንዲሰጥል፤ የአባታችንን ነፍስ ዕረፍተ-ነፍስ ሰጥቶ ከቅዱሳን ሐዋርያት ጋር እንዲያሳርፍልን፤ ለኛም ለጠቅላላው ሕዝበ-ክርስቲያን የብጹዕነታቸውን ጸሎት፣ በረከትና ሀብተ-ረድኤት እንዲያድለን የእግዚአብሄር መልካም ፈቃዱ ይሁንልን አሜን ።

ከሊቀ-ካህናት አስተርአየ ካሣ እንዲሁም በጀርመን ሃገር በቪስባደንና አካባቢው ከሚኖሩ ምዕመናንና ምዕመናት ።

PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com